## ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ ዓርብ የሚቀርብ

# ፐብሊክ ሰርቪስ አውቶቡስ ያለምንም አደጋ አገልግሎት የመስጠት ተምሳሌት

**መርድ ክፍሉ**

ፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በፌዴራልና በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የፐብሊክ ሰርቪስ መስሪያ ቤቶች ለሚሰሩ የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች በሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓቶች እንዲሁም ከሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ውጪ፣ በበዓላትና ዕረፍት ቀናት ለሌላው የህብረተሰብ ክፍል የህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በተመጣጣኝ ታሪፍ የሚሰጥ ወጪውን በመቀነስና ገቢውን በማሳደግ ከተቋቋመበት ዓላማ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን አገልግሎቶችን የሚሰጥ ድርጅት ነው፡፡ ፐብሊክ ሰርቪስ አገልግሎት ድርጅት የመንግስት ሰራተኛውን ለማገልገል ብቃት ያላቸው የባስ ካፒቴኖችን አሰማርቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ በመስከረም 15 ቀን 2014 ዓ.ም የመንግስት ሰራተኛው በብቃትና ምንም አይነት አደጋ ሳያደርሱ እያገለገሉ ያሉትን የባስ ካፒኖች ሸልሟል፡፡ ባስ ካፒቴኖቹ ስድስት ዓመት፣ አምስት ዓመት እንዲሁም አራት ዓመት ያለምንም አደጋ ያሽከረከሩ የወርቅ፣ የብርና የነሀስ ሜዳሊያ ተሸላሚ ሆነዋል፡፡

ባስ ካፒቴን ታጠቅ ነጋሽ በፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት ለስድስት ዓመታት ያለምንም አደጋ ያሽከረከሩ በመሆናቸው የወርቅና የዋንጫ ተሸላሚ ሆነዋል፡፡ እሳቸው እንደሚናገሩት፣ የሹፍርና ህይወት ከጀመሩ ጀምሮ ያለ ምንም አደጋ እዚህ ደርሰዋል፡፡ ሁሌም ጠዋት ሲወጡ ለአምላካቸው ፀሎት አድርሰው ሲሆን በቻሉት አቅም ሞገደኛ ሹፌር ላለመሆን ጠንክረው ይሰራሉ፡፡ ባላቸው ክህሎት ህብረተሰቡን እያገለገሉ ይገኛሉ፡፡

በመስሪያ ቤቱ ሰባት ዓመታትን እንዳገለገሉ የሚናገሩት ባስ ካፒቴን ታጠቅ፣ በተመደቡበት መስመር መንግስት ሰራተኛውን በአግባቡ እያስተናገዱ መሆናቸውን ይጠቅሳሉ፡፡ በየስድስት ወሩ በሚደረጉ ቅያሬዎች ሰራተኛውን እያገለገሉ መሆናቸውን ይጠቁማሉ፡፡ በሰሚት ኮንደሚንየም፣ በመገናኛ፣ በካሳንቺስ፣ በአየር ጤና እንዲሁም ሌሎች ቦታዎች ላይ የሰርቪስ አገልግሎት መስጠታቸውን ይናገራሉ፡፡

በወጣትነት እድሜያቸው ወደ ሹፌርና ዓለም ለሚገቡ ሞገደኛ ሹፌር ላለመሆንና እንደየመንገዱ ሁኔታ በርጋታ የሚነዱበት ሁኔታ ሊፈጥሩ እንደሚገባ ይናገራሉ፡፡ በከተማዋ ያለው የመንገድ ሁኔታ በመሻሻል ላይ ያለ በመሆኑ በመተሳሰብ ላይ በተመሰረተ ሁኔታ ማሽከርከር አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ከአደጋ የፀዳ አገልግሎት ለመስጠት ከስሜታዊነት መውጣት አለባቸው፡፡ በብስጭትና በንዴት ሰዓት መኪና ከማሽከርከር ቢቆጠቡ መልካም እንደሚሆን ባስ ካፒቴን ታጠቅ ምክራቸውን ይሰጣሉ፡፡

ባስ ካፒቴን ታጠቅ፣ መስሪያቤታቸው ላበረከቱት የስራ እንቅስቃሴ የሰጣቸው እውቅና እንዳስደሰታቸው ይናገራሉ፡፡ ባበረከቱት አስተዋፅኦ የተሰጣቸው የምስጋና ሜዳሊያና ዋንጫ ለበለጠ የስራ እንቅስቃሴ እንደሚያነሳሳቸው ያስረዳሉ፡፡ በሚሰሩባቸውም መስመሮች ላይ ሰርቪስ ከሚጠቀሙ ሰራተኞች ጋር ተግባብተው እየሰሩ መሆናቸውን ያመለክታሉ፡፡

ሌላኛው በመስሪያቤቱ በሹፍርና እያገለገለ ያለውና ለአምስት ዓመታት ያለምንም አደጋ በማሽከርከሩ የብር ሜዳሊያ የተሸለመው ወጣት ባስ ካፒቴን እስራኤል እኩሞ ነው፡፡ ባስ ካፒቴን እስራኤል ወደ ፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ከሰባት ዓመት በፊት መግባቱን ይናገራል፡፡ በወቅቱ አነስተኛ መኪናዎችን ያሽከረክር የነበረ ሲሆን በስራውም በተደጋጋሚ መሸለሙን ያስታውሳል፡፡

ወደ ሰርቪስ አገልግሎት ከተመደበ አንድ ዓመት እንደሆነው የሚናገረው ባስ ካፒቴን እስራኤል፣ ሰርቪስ በሚሰጥበት ወቅት ምንም አይነት አደጋ እንዳላደረሰ ይጠቁማል፡፡ በስራውም ውጤታማ ስለነበር የብር ሜዳሊያ ለመሸለም መብቃቱን ያመለክታል፡፡ ማንኛውም ሹፌር በሚያሽከረክርበት ወቅት ብዙ ነገሮች የሚያጋጥሙ ሲሆን ሁሉንም ሁኔታ በተረጋጋ መንፈስ መመልከትና ማሳለፍ እንደሚጠይቅ ያስረዳል፡፡

ምንም አይነት አደጋ ሳያደርሱ ማሽከርከር ትልቅ የህሊና እርካታ እንደሚሰጥ ባስ ካፒቴን እስራኤል ይናገራል፡፡ በአገሪቱ በመኪና አደጋ የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መሆኑ በተለያዩ መንገዶች እየተገለፀ ነው፡፡ ይህን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መኪና በሚያሽከረክሩበት ወቅት ከማንኛውም ሃሳብ በፀዳ መልኩ ማገልገል እንዳለባቸው ይናገራል፡፡ ሹፌሮች ተረጋግተው ማሽከርከር በሚገባቸው ቦታዎች ላይ ተጠንቅቀው እንዲያሽከረክሩ ምክሩን ይሰጣል፡፡

ፐብሊክ ሰርቪስ የትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ለሰራተኞቹ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራ መሆኑን የሚጠቅሰው፣ ባስ ካፒቴን እስራኤል መስሪያቤቱ በራሱ ሰራተኞችን በማሰልጠን እድገት እንዲያገኙ የሚያደርግ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ከስር የሚገኙ ሰራተኞች እድገት ስለሚሰጥ ሰራተኛው ኃላፊነት ተሰምቶት እንዲሰራ የሚያደርግ በመሆኑ እሱ ደስተኛ በሆነ ስሜት ስራውን እያከናወነ መሆኑን ይጠቅሳል፡፡

ለአራት ዓመታት ያለምንም አደጋ በማሽከርከር የነሀስ ሜዳሊያ ተሸላሚ የሆነው ባስ ካፒቴን ቢንያም ነጋሽ፣ በፐብሊክ ሰርቪስ ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ውስጥ ከምስረታው ጀምሮ እያገለገለ መሆኑን ይናገራል፡፡ ባጋጣሚ ከመስሪያ ቤቱ ለቆ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ግን ተመልሶ እያገለገለ እንደሚገኝ ይገልፃል፡፡ በመስሪያ ቤቱ ባገለገለባቸውና አሁንም እያገለገለ ባለበት ወቅት ምንም አይነት አደጋ አለማድረሱን ያስረዳል፡፡

ማንኛውም ሹፌር ለስራ ሲወጣ አዕምሮውን ለስራ ዝግጁ አድርጎ ከቤት መውጣት አለበት፡፡ ሌላው አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት አዕምሯቸውን እዛው መኪና ውስጥ ማድረግ እንዳለባቸው ይናገራል፡፡ ማንኛውም በሹፍርና ውስጥ ያለ ሰው በግል ህይወቱ የተለያዩችግሮችቢያጋጥሙትምእሱንበመርሳትበአግባቡ አገልግሎት መስጠት እንዳለበት ይጠቁማል፡፡ የሚሰራበት መስሪያ ቤት ሰራተኛውን ለማበረታታት እየወሰደ ያለው እርምጃ ጥሩ መነሳሳት እደሚፈጥር ባስ ካፒቴን ቢንያም ይናገራል፡፡ እንደዚህ አይነት ሽልማቶች ሰራተኛው ተግቶ እንዲሰራ እንደሚያደርግ ይጠቅሳል፡፡ ሁሉም አሽከርካሪ ሰላም ሆኖ ከቤቱ ከወጣ ውጤታማ እንደሚሆን ያስረዳል፡፡

በእውቅና ፕሮግራሙ ላይ ንግግር ያደረጉት የፐብሊክ ሰርቪስ አገልግሎት ድርጅት ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍሬህይወት ትልቁ፣ ድርጅቱ በ2013 ዓ.ም 430 ተሽከርካሪዎች በመመደብ በቀን ከ100 ሺህ በላይ ለሚሆኑ የፐብሊክ ሰርቪስ ሰራተኛ የትራንስፖርት ተጠቃሚዎች አገልግሎት መስጠት መቻሉን ይናገራሉ፡፡ አገልግሎት መስጠት ብቻም ሳይሆን አገልግሎቱ ከአደጋ የፀዳ እንዲሆን የተሰጣቸውን ስልጠና ወደ ተግባር በመቀየር እየደረሰ ያለውን የመንገድ ላይ የትራፊክ አደጋ ለመከላከል የበቁ አሽከርካሪዎችን ማበረታታት በአርዓያነቱ የሚገለፅ ተግባር መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡

ድርጅቱ ህግ አክባሪ አሽከርካሪዎችን ከማፍራት እና ከማበረታታት ጀምሮ በርካታ ጥረቶችን ማድረግ የተቻለ በመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለስምንተኛ ጊዜ የኢትዮጵያ ጥራት ሽልማት ድርጅት ባካሄደው ውድድር የዋንጫ ተሸላሚ መሆን ተችሏል፡፡ በእውቅና ፕሮግራሙ 223 የአውቶቡስ አሽከርካሪዎች ከሰርተፍኬት ጀምሮ የተለያዩ ሽልማቶች እንዲሰጣቸው ተደርጓል።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚቀርብ

# የትምህርቱን ዘርፍ ለመደገፍ የሚደረገው ጥረት

**እየሩስ ተስፋዬ**

የትምህርቱ ዘርፍ ውጤታማ የሚባል ለውጥ እንዲያመጣ መንግስት የራሱን ድርሻ በመወጣት ላይ ይገኛል። ባለፉት ሦስት ዓመታት ለውጡ ከመጣ በኋላም ቢሆን አዲሱን የትምህርት ፍኖተ ካርታ ከማዘጋጀት ጀምሮ በኮሮና ምክንያት የተዘጉ ትምህርት ቤቶች ዳግም ተከፍተው ተማሪዎች ወደ ትምህርት ገበታቸው እንዲመለሱ በርካታ ሥራዎች ተሰርተዋል። ውጤታማ ነበሩ።

ይሁን እንጂ የትምህርቱ ዘርፍ ከሚገጥሙት ፈተናዎች ለመውጣት የብዙዎችን ተሳትፎና ድጋፍ የሚጠይቅ እንደመሆኑ ከአጋር አካላት ጋር በብርቱ መሥራትም አጠያያቂ አይደለም። ይህን ታሳቢ በማድረግ መንግስት የበኩሉን፤ ለጋሽ ደርጅቶችም የድርሻቸውን ከመስጠት ወደ ኋላ አላሉም።

እንደሚታወቀው በያዝነው ዓመት በተለያዩ ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ትምህርት ለማስጀመር የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በመሰራት ላይ እንደሆነ የሚታወቅ ሲሆን ትምህርት ቤቶችን ለመማር ማስማር ሂደት ከማዘጋጀት ጀምሮ ትምህርት ቤቶችን በማደስ እና በማጽዳት ምቹ እንዲሆኑ ተደርገዋል።

ትምህርት ቤቶች ዝግጁ ይሁኑ እንጂ አቅማቸው ደካማ የሆኑ ተማሪዎች ደግሞ የትምህርት መጀመር ዜና ሲሰማ ጭንቀት ውስጥ የሚገቡት ተማሪዎችም በርካታ ናቸው። እንዲህ አይነቱን ችግር ለመቅረፍ ከማሰብ ረገድም በባለፈው 2013ዓ.ም የአቅመ ደካማ ተማሪዎች ችግርን ለመቅረፍ በማሰብ መንግስት ለተማሪዎች የደንብ ልብስን ጨምሮ የተለያዩ የመማሪያ ቁሳቁሶችን ድጋፍ ማድረጉ አይረሳም። ድጋፉም አቅም ለሌላቸው ተማሪዎች እና ለወላጆቻቸውም ቢሆን እፎይታን የፈጠረ




ነበር።

በአሁኑ ወቅትም ቢሆን እንዲህ ያሉ መልካም ሥራዎች ቀጥለዋል። በያዝነው ሳምንት የቻይና ፋውንዴሽን ከአሊባባ ጋር በመተባበር ለ20 ሺ የተማሪዎች ቦርሳ ለትምህርት ሚኒስቴር ድጋፍ አድርጓል። ድጋፉ 118 ሺ ቦርሳዎችን ለመደገፍ ቃል ከተገባው ውስጥ የመጨረሻው ዙር ነው።

ይህንን ድጋፍ በተመለከተም የትምህርት ሚኒስትር ዶክተር ኢንጂነር ጌታሁን መኩሪያ የቻይና መንግስት የኮቪድ ወረርሽኝ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ የህክምና ባለሙያዎችን ከመላክ ጀምሮ እስከ ክትባት ድረስ ከፍተኛ ድጋፍ ሲያደርግ መቆየቱን ተናግረዋል።

በኢትዮጵያ የቻይና አምባሳደር ዋና ጻሃፊ ኬ ሊዮ በበኩላቸው ቻይና ከድህነት ወጥታ በዓለም በኢኮኖሚ መሪ ከሆኑ አገራት ተርታ የተሰለፈችው ለትምህርት ልዩ ትኩረት በመስጠቷ እንደሆነ በመግለጽ፤ በመሆኑም ኢትዮጵያ በትምህርት ዘርፍ በምትሰራቸው ስራዎች ቻይና ድጋፏን አጠናክራ ትቀጥላለች።

ድጋፉ በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ ተማሪዎች የሚከፋፈል ሲሆን የኦሮሚያና የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮዎች ድጋፉን የተረከቡ ሲሆን ሌሎች የክልል ትምህርት ቢሮዎች በቀጣይ ድጋፉን ተረክበው የሚያከፋፍሉ ይሆናል።

የኮቪድ 19 ክፉኛ ከፈተናቸው ዘርፎች መካከል የትምህርቱ ዘርፍ በቀዳሚነት ይጠቀሳል። በዚህም ሳቢያ በርካታ ተማሪዎች፣መምህራን፣ የትምህርት ቤት አስተዳደሮችና ሠራተኞች ከትምህርት ቤታቸውን እንዲቀሩ አስገድዷቸው ነበር።

ይሁን እንጂ ትምህርት ቤቶች ጤና ሚኒስቴር ያወጣውን መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ ውጤታማ የሚባል ሥራ ተሰርቷል።

በአሁኑ ወቅትም ቫይረሱ የሚያደርሰውን ጫና ታሳቢ በማድረግ የቻይና መንግስት ለትምህርት ሴክተሩ ለኮቪድ 19 መከላከል አገልግሎት የሚውል 300 መቶ ሺህ ክትባቶችን ድጋፍ ማድረጉም አይዘነጋም፡፡

በቻይና መንግስት ለትምህርት ሴክተሩ የተደረገው ድጋፍ በሽታው ይበልጥ በተባባሰባቸው ክልሎች ላይ መድረስ እንደሚያስችል ፤ እንዲሁም በሽታውንም ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት ይበልጥ እንደሚያግዝም የትምህርት ሚኒስትሩ ገልጸው፤ ድጋፉ በትምህርት ዘርፉ ላይ ሊኖር የሚችለውን የኮቪድ 19 ስርጭትን ለመከላከል ከፍተኛ አስተዋጾ እንዳለውም አስረድተዋል።

የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ እንደገለጹት ለበሽታው ይበልጥ ተጋላጭ ከሆኑ ማህበረሰብ ክፍሎች መካከል መምህራን ናቸው፡፡ መምህራን ክትባቱን እንዲወስዱ መደረጉ በሽታውን ከመከላከል ባለፈ ስርጭቱ ወደ ከፋ ደረጃ እንዳይደርስም ያግዛል፡፡

የቻይና መንግስት ባደረገው ድጋፍ 150 ሺህ መምህራን ለመከተብ ያስችላል፡፡ መምህራን እና የአስተዳደር ሠራተኞች ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ክትባቱን ያገኛሉ፡፡

ለትምህርቱ ዘርፍ እድገት የሁሉም ሠው ድርሻና ድጋፍ ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ ኃላፊነቱን መወጣትም ይገባል፡፡